# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

# Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ. ም

## የፕሪቶሪያውን ስምምነት ማስፈጸም ጥንቃቄ ያሻዋል

ከሃምሳ ዐመታት የዘረኝነትና የመከፋፈል ሤራና ድርጊት በኋላ፣ ከ27 ዐመታት የዕመቃና አፈና አገዛዝ በኋላ፣ ከሁለት ዓመታት የጦርነት ግድያ፣ ዕልቂት፣ ዝርፊያና ውድመት በኋላ፣ በተለይ በትግራይ፣በአፋር፣ በጎንደር፣ በወሎ ከሚኖረው ህዝብ ሚሊዮኖች ተፈናቅለው በርሃብ፣ በርዛት በስደት ለስቃይ ከተዳረጉና፣ ገና በውል ያልታወቁ ወገኖቻችን ለሞት ከተዳረጉ በኋላ ህ.ወ.ሓ.ት. ዕውን ሠላምን ከልቡ አምኖ ይቀበል ይሆን?? በኢትዮጵያውያን በኩል፣ መላው ህዝብ፣ ገዥው ፓርቲና ተፎካካሪ ፓርቲዎችም ጭምር ሠላምን አጥብቀው እንደሚፈልጉ ዕሙን ነው። በደቡብ አፍሪቃ ዋና ከተማ በፕሪቶሪያ በኢትዮጵያ መንግሥትና በተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ (ተሓህት) መካከል የተደረገው ድርድር የሚያሳየው ሁላችንም ያለንን የሠላም ፍላጎት ነው እንላለን። በአደራዳሪነት የተሳተፉትም በኢትዮጵያችን፣ በምሥራቅ አፍሪካና በመላው አፍሪካ ሠላም እንዲሰፍን በመፈለግ፣ የምእራባውያኑን ጣልቃገብነት መከላከልንም በግንዛቤ በማስገባት፣ የማደራደሩን ተግባር በማካሄዳቸው ሊመሰገኑ ይገባል። ሠላም እንዲወርድ ስምምነት ላይ መደረሱ በተለያዩ የዜና አውታሮች ተዘግቧል፡፡ ስምምነቱ ለአገራችን ዘላቂ ሰላም የሚያመጣ ከሆነ የምንመኘው ነውና እንደግፈዋለን። የሀገር ልማት ያለ ሠላም መስፈን ሊመጣ እንደማይችል ስለምናምን፣ ዘላቂነት ያለውና አስተማማኝ ሠላም እንዲሰፍን ያለጥርጥር ኢሕአፓ ይፈልጋል። በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ስምምነት ላይ በመደረሱ ደስ ቢለውም ህወሓትን ከልቡ ማመን ግን ዛሬም ይከብደዋል።

ጦርነት በርግጥ አውዳሚ ነው። ምንጊዜም ችግሮችን በሠላማዊ መንገድ መፍታት ሲቻል ጦርነት በችግሮች መፍቻነት ተመራጭ አይሆንም። የሰውን ሕይወት ይቀጥፋል፣ ሕዝብን ከቀዬው ያፈናቅላል፣ ንብረትንም ያወድማል፡፡ ሠላምን ያሳጣል፣ ያለሠላም ደግሞ ዕድገትና ልማት ሊገኙ በፍጹም አይችሉም። ሕዝብ እንደ ሕዝብ ማንነቱ ሲደፈርና በግፍ ሲጨፈጨፍ፣ መብቱ ሲረገጥ፣ ነፃነቱን ሲገፈፍ፣ የአገሩ ሉዓላዊነትና አንድነት አደጋ ላይ ሲወድቁበት፣ የአገሩን ድንበር ለመጠበቅ፣ እራሱን ለመከላከል፣ ነፃነቱንና መብቱን ለማስከበር ጦርነት ውስጥ ይገባል እንጂ፣ ጦርነት ዝም ብሎ የሚገባበት አይደለም፡፡ ስለሆነም ባለፉት ሁለት ዓመታት በአገራችን የሰሜኑ ክፍል ውስጥ የብዙ ወገኖቻችን ሕይወት ከቀጠፈና በብዙ ሺህ የሚቆጠርን ሕዝብ ቤትና ንብረት አልባ ካደረገ አሰቃቂ ጦርነት ወጥቶ ሰላምን ለማስፈን በተደጋጋሚ በመንግሥት በኩል የተደረገውን ትልቅ ጥረት ኢ ሕ አ ፓ በአንድ በኩል እያደነቀ፣ እስከዛሬ በሌላው ወገንና ደጋፊዎች መሠሪነት የጥረቶቹን ሳይሳኩ መቅረትም በምሬት ትምህርት ነውና ይገነዘባል፡፡

Phone: 0251 911 400 982 **e-mail: eprp@eprp-ihapa.com**

እስከዛሬ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል እየተካሄደ ያለው ጦርነት፣ ተሓህት ትግል ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደርስ የነበረው ዘግናኝና አሰቃቂ ግፍ ሳይበቃው፣ የዛሬ ሁለት ዐመት በሰሜን ዕዝ ላይ ጭፍጨፋ በማካሄድ ህወሓት የጀመረው ጦርነት፣ ካደረሰው ውድመት በላይ የአገራችንን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነትን በቀጥታ ያስደፈረ ተግባር ነበር። ይህ ኢትዮጵያን ያዋረደ አሳፋሪ ተግባር ነው። እስከዛሬ የቀጠለው መላው ሕዝባችን አገራችን ላይ የተደቀነን ጥፋት፣ ውድመት፣ ሞትና ስቃይ ለመታደግ እያካሄደው ያለ የሞትና የሽረት ጦርነት ነው፡፡ ከዘግናኝና አሰቃቂ በጭቆና ስር ከመማቀቅ ኑሮ፣ የዘላለም መራራ ሕይወት ለመውጣት፣ እንዲሁም አባቶቻችንና እናቶቻችን ደማቸውን አፍስሰው፣ አጥንታቸውን ከስክሰው ያስረከቡንን የአገራችንን ሕልውና ለማስጠበቅ ሳንወድ በግድ የገባንበት ጦርነት ነው፡፡

ሕዝባችንና ጥምር ኃይሉ ከፍተኛ የሕይወት መስዋዕትነት በመክፈል ልቡን በትዕቢት የወጠረን ቡድን ሊቋቋመው ወዳልቻለው መቀመቅ ውስጥ አስገብቶ ዛሬ የሠላም ስምምነት ተቀብያለሁ ቢልም፣ እስከዛሬ ያሳያቸው የነበሩትን ተደጋጋሚ ክህደቶችና አጠቃላይ ባኅሪውን ይተዋል ብለን ማመን ስለከበደን፣ ስምምነቱን ብንወደውም በተግባሩ እስከሚፈጽም መጠበቅን እንመርጣለን። እስከዚያም የፖለቲካ ሃይሎች ሁሉ በጥንቃቄ እንዲጠባበቁ እንመክራለን።

በተለይም ልክ የዛሬ ሁለት ዐመት፣ የትግራይን አካባቢ ከሃያ ዓመታት በላይ ሲጠብቅና የትግራይን ነዋሪዎች ሲረዳ የነበረውን የመከላከያ ሠራዊት፣ በጠፍ ሌሊት፣ የካደና የጨፈጭ፡ እፈ ቡድን መሆኑ ለአፍታም ሊዘነጋ አይገባም፡፡ ስለሆነም ተሓህት በማንኛውም ጊዜ ስምምነቱን አፍርሶ ወደ ነበረበት ሊመለስ የሚችል ኃይል ሊሆን ይችላልና መንግሥት የስምምነቱን ተግባራዊነት በጥንቃቄና በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መፈጸሙን ጽኑ ክትትል ማድረግ አለበት ይላል ኢሕአፓ፡፡

ወደ ስምምነቱ ዝርዝር ስንገባ የተወሰኑ መብራራት ያለባቸው ነጥቦች መኖራቸውን ተገንዝበናል። በግልጸኝነት መጓደል ምክንያት የሕዝባችን ሙሉ ድጋፍና ተሳትፎ ከሌለ፣ ኢሕአፓ አገራችን ዳግም ልትወጣ ወደማትችለው አደገኛ አዘቅት ውስጥ ልትገባ ትችል ይሆናል የሚል ከፍተኛ ስጋት አለው፡፡ ከዚህ ሌላ የአገራችንን ሉዓላዊነት ለማስከበር፣ አንድነቷን ለማስጠበቅ ህወሓትን ለማንበርከክ ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈለውን የጥምር ኃይላችን ጀግኖች በሙሉ፣ ለሀገርና ለወገን ቤዛ በመሆን ላፈሰሱት ደምና ለከሰከሱት አጥንት፣ ለከፈሉት በእንግልት፣ ርሃብና ጥምና አካል-መጉደል ከባድ መስዋዕት፣ በዚህ አጋጣሚ ትልቅ ክብር እንሠጣለን!! ሁሌም ልንከባከባቸው ይገባናል እንላለን፡፡

የተባበር ኃይል ምንጊዜም አቸናፊ ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን ለሚጠሉን ሁሉ በተለይም ለባዕዳኑ ጋላቢዎች አንዘናጋላቸው!!

Phone: 0251 911 400 982 e-mail: eprp@eprp-ihapa.com